በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የካ ክ/ከተማ

የ6ኛ ክፍል የሒሳብ ሞዴል ፈተና

ግንቦት 2015ዓ.ም

የጥያቄ ብዛት: 30 የተፈቀደው ሰዐት: - 1 ሰዐት

አጠቃሊይ ትዕዛዝ

ይህ ሂሳብ ፈተና ነው፡፡ በዚህ ፈተና ውስጥ 30 ጥያቄዎች ተካተዋል፣ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የሆነውን አማራጭ የያዘውን ፊደል በመመረጥ የመልስ መስጫ በተሰጠው ወረቀት ላይ በማጥቆር መልስ ይሰጣል፡፡ በፈተና ላይ የተሰጡትን ትእዛዞች በጥንቃቄ በማንበብ ፈተናውን መስራት ይጠበቅባችኋል፡፡ መልስ የሚሰጠው ከፈተናው ጋር በተያያዘው የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ ነው ፤በመልስ መስጫው ላይ ትክክለኛውን መልስ የሚጠቆረው በእርሳስ ብቻ ነው፣ ትክክለኛው መልስ በማጥቆር ሲሰራ የማጥቆር የተፈቀደው ቦታ በሙሉ በሚታይ መልኩ በደንብ መጥቆር አለበት፤ የጠቆረውን መልስ ለመቀየር ቢፈለግ በፊት የጠቆረውን በደንብ በማጥፋት መጽዳት አለበት፡፡

ፈተናውን ሰረቶ ለመጨረስ የተፈቀደው ሰአት 1 ሰአት ነው፡፡ ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተሰጠው ሰዓት ሲያበቃ ለመስሪያነት የምንጠቀምበትን የመጻፊያ እርሳስ ማስቀመጥ እና ፈተናውን መስራት ማቆም አለብን፡፡ ፈተናው እንዴት እንደሚሰበሰብ በፈታኙ/ኟ እስከሚነገር ድረስ በቦታችን ተቀምጠን መጠበቅ አለብን፡፡

መኮረጅ ወይም በፈተና ሰአት የፈተናን ህግ የማያከብር ተፈታኝ ፈተናው አይያዝለትም፤ ፈተናውን እንዳይፈተንም ይደረጋል፡፡

ፈተናውን መስራት ከመጀመራቹሁ በፊት በመልስ መስጫው ላይ መሙላት የሚገባውን መረጃ ሁሉ በጥንቃቄ መሙላት አለበት፡፡

**ፈተናውን መስራት ጀምሩ ሳይባል መጀመር አይፈቀድም !**

**መመሪያ አንድ ፡-የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ**

1. ከሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮን ውስጥ ተጋማሽ ቁጥር የሆነው የትኛው ነው ?
   ሀ/ 3243 ለ/ 4789 ሐ/ 8075 መ/ 4786
2. ከሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮን ውስጥ ለስድስት ተካፋይ የሆነው የቱ ነው ?
   ሀ/ 8156 ለ/ 3627 ሐ/ 7254 መ/ 9670
3. ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች መካከል ትክክል የሆነው የትኛው ነው ?
   ሀ/ 12 የ128 አካፋይ ነው፡፡ ሐ/ 4 የ154 አካፋይ ነው፡፡
   ለ/ 12 የ132 አካፋይ ነው፡፡ መ/ 9 የ143 አካፋይ ነው፡፡
4. ከሚከተሉት መካከል የ240 ብቸኛ ትንትን የሆነው የትኛው ነው?
   ሀ/ $2^4 \times 3 \times 5$ ለ/ $2^3 \times 3^2 \times 5$ ሐ/ $3^2 \times 2 \times 5$ መ/ $2^3 \times 5^2 \times 3$
5. ከሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች ውስጥ የ120 እና የ84 ትልቁ የጋራ አካፋይ የሆነው የቱ ነው
   ሀ/12 ለ/ 18 ሐ/16 መ/ 24
6. ማርታ በ12 ጀምራ በ6 ልዩነት መቁጠር ጀመረች ብቱካን ደግሞ በ10 ጀምራ በ5 ልዩነት መቁጠር ያዘች ማርታ እና ብርቱካን በቆጠራው የሚገናኙትተ የመጀመሪያው ተመሳሳይ ቁጥር ስንት ነው ?
   ሀ/ 120 ለ/ 30 ሐ/ 60 መ/ 150
7. ከሚከተሉት መካከል የ $\frac{112}{72}$ ዝቅተኛ ሒሳባዊ ቃል የሆነው የቱ ነው ?
   ሀ/ $\frac{14}{18}$ ለ/ $\frac{7}{9}$ ሐ/ $\frac{14}{9}$ መ/ $\frac{28}{18}$
8. ከሚከተሉት ውስጥ ትክክል የሆነው የቱ ነው?
   ሀ/ $2\frac{1}{3} = 3.75$ ለ/ $4\frac{1}{2} = 4.5$ ሐ/ $\frac{7}{4} = 1.75$ መ/ $3\frac{1}{4} = 3.75$
9. $\frac{23}{50}$ ይህ ክፍልፋይ በፐርሰንት ሲገለፅ ስንት ነው?
   ሀ/ 66% ለ/ 23% ሐ/ 50% መ/ 46%

10 .ከሚከተሉት ውስጥ እውነት የሆነው የትኛው ነው?
   ሀ/ $\frac{12}{13} < \frac{9}{11} < 0.34$ ሐ/ $\frac{1}{9} < \frac{2}{7} < \frac{5}{3} < \frac{7}{2}$
   ለ/ $0.5 < \frac{1}{4} < 0.8 < \frac{4}{5}$ መ/ ሁሉም ትክክል ነው

11. አልማዝ ከነበራት 140 ብር ውስጥ 45% የሆነውን መፅሐፍ ገዛችበት ፡፡አልማዝ ለመፅሐፉ ስንት ብር አወጣች?
   ሀ/ 54 ለ/ 63 ሐ/ 45 መ/48
12. $\frac{1}{4} \times 0.5$ = ____________
   ሀ/ $\frac{1}{8}$ ለ/ $\frac{5}{10}$ 22 ሐ/ $2\frac{5}{20}$ መ/ $\frac{5}{8}$

13 .ከሚከተሉት ውስጥ ትክክል የሆነው የቱ ነው?
   ሀ/ $2\frac{1}{2} \div 0.25 = 25$ ለ/ $4.2 \times 5.4 = 22.68$
   ሐ/ $5.6 \times 3\frac{1}{4} = \frac{91}{5}$ መ/ $7\frac{1}{3} \div \frac{4}{12} = \frac{22}{36}$
14. የአንድ የመኪና ፍጥነት እና የሚወስደው ጊዜ?
   ሀ/ ርቱዕ ወደረኛ ለ/ ኢ-ርቱዕ ወደረኛ ሐ/ ሀ እና ለ መ/ መልስ የለም

15. ቀ− 0.5 =2.50 ቢሆን የተለዋዋጭ ዋጋ ተክቶ ዓረፍተ ነገሩን እውነት የሚያደርገው ሙሉ ቁጥር የቱ ነው?
   ሀ/ 2.3 ለ/ 23 ሐ/ 3.3 መ/ 33

16. አንድ መኪና በሰዓት 60 ኪሎ ሜትር ቢጓዝ 240 ኪ.ሜ በስንት ሰዓት ይጓዛል?

ሀ/ 6 ለ/ 8 ሐ/ 12 መ/ 4

17. ቀ ከ ሸ ጋር ኢ-ርዕቱ ወደረኛ ናቸው ሸ =4 **ሲሆን** ቀ= 12 ይየሆናል ቀ= 6 ሲሆን የሸ ዋጋ ስንት ነው?

ሀ/ 48 ለ/ 3 ሐ/ 16 መ/ 8

18. ከሚከተሉት ውስጥ የጎነ ሶስት ምስል የጎን ርዝመት የሚሆኑት የትኞቹ ናቸው?

ሀ/ 2፣3፣1 ለ/ 4፣2፣6 ሐ/ 8፣8፣8 መ/ 7፣3፣4

19. ከሚከተሉት መካከል ትክክል ያልሆነው የትኛው ነው

ሀ/ የካሬ ዲያጎናሎች እኩል ናቸው ሐ/ የሬክታንግ ዲያጎናሎች ሲቋረጡ $90^0$ ይሆናል

ለ/ የሬክታንግል ተቃራኒ ጎኖች እኩል ናቸው መ/ የካሬ ሁሉሙ ጎኖች እኩል ናቸው

20 .ከሚከተሉት ውስጥ ስለ ሬክታንግል ፒራሚድ ትክክል የሆነው የቱ ነው?

ሀ/ 12 ጠርዞችና 5 ገፆች አሉት ሐ/ 12 ጠርዞችና 8 ገፆች አሉት

ለ/ 8 ጠርዞችና 5 ገፆች አሉት መ/ 9 ጠርዞችና 6 ገፆች አሉት

21. ሬዲሱ 3 ሳ.ሜ የሆነ ክብ ዲያሜትሩ ስንት ሳ.ሜ ይሆናል?


ሀ/ 6 ሳ.ሜ ለ/ 3 ሳ.ሜ ሐ/ 9 ሳ.ሜ መ/ 1 ሳ.ሜ

22. ሁለት ትይዩ እና እኩል መሰረት ያለው ጠጣር ምስል ምን ይባላል?

ሀ/ ፒራሚድ ለ/ ፕሪዝም ሐ/ ሲሊደር መ/ ኩብ

23. ከሚከተሉት ውስጥ ሹል አንግል ጎነ-ሶስት የሆነው የትኛው ነው?

ሀ/ $45^0$፣ $90^0$ ፣$45^0$ ለ/ $110^0$ ፣$35^0$ ፣$35^0$ ሐ/ $60^0$፣$75^0$፣$50^0$ መ/ $120^0$፣$35^0$ ፣$25^0$




ምስል 3.2


24.ከላይ በምስል 3.2 ከቀረቡት ፍርቅ ውስጣዊ አንግል የሆነው የቱ ነው?

ሀ/ <ሠ እና <2 ለ/ <መ እና < 1 ሐ/ <ሀ እና<2 መ/ <መ እና<2

25. በምስል 3.2 ከተሰጠው ውስጥ የ<1 ልኬት ስንት ነው?

ሀ/ $75^0$ ለ/ $95^0$ ሐ/ $105^0$ መ/ $85^0$

.




ምስል 3.3


26. ከላይ በምስሉ 3.3 ከተሰጠው ክብ ላይ ውስን ቀጥታ መስመር መሠ ምን ይወክላል?
ሀ/ ኮርድ ለ/ ዲያሜትር ሐ/ እምብርት መ/ ሀ እና ለ

27. በምስል 3.3 ከተሰጠው ክብ ላይ ራዲየስን የሚወክለው የቱ ነው?
ሀ/ውስን መስመር መሠ ለ/ ውስን መስመር ቀመ ሐ/ውስን መስመር ቀወ መ/ውስን መስመር ለሠ

28. የ18፤16፤24፤30፤ቀ እና10 ሚዲያን 20 የሚሆነው በመረጃ ውስጥ የሚካተተው ቁጥር ስንት ነው?
ሀ/ 16 ለ/ 22 ሐ/ 30 መ/ 20

ከተራ ቁጥር29 እስከ 30 ድረስ ያሉትን ጥያቄዎች በተሠጠው ፓይቻርት መሠረት መልስ ስጡ፡፡

ተማሪ ሳራ በአራት የትምህርት ዓይነት ተፈትና ያገኘችዉ ጠቅላላ ድምር 340 ቢሆንና በእያንዳንዱ የትምህርት አይነት ያገኘችዉ ዉጤት መሠረት እንደሚከተለው በፓይቻርት ተገልጾዋል፡፡




29. ከላይ በተሠጠው ፓይቻርት መሠረት ተማሪ ሳራ በሒሳብ ትምህርት ያስመዘገበችው ውጤት ስንት ነው?
ሀ/ 80.3 ለ/ 96.3 ሐ/76.5 መ/ 86.9

30. ከላይ በተሠጠው ፓይቻርት መሠረት ተማሪ ሳራ ያገኘችው የፈተና ውጤት ሬንጅ ስንት ነው?
ሀ/ 16 ለ/ 21 ሐ13.3 መ/ 17.5